ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ግንቦት 27 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

## ያለማወቅ ጉዳትና የግንጠላ መዘዙ

ከመናገር በፊት ማወቅ መመራመር የሚለው ዘንድሮ ተረስቶ እንዳመችና አፍ እንዳመጣ መናገር መተቸት፤ አልፎም ማውገዝ ተለመደና አያሌ ጽንሰ ሀሳቦች፤ክስተቶችና መፈክሮች ወይም መርሆዎች ድብልቅልቃቸው ወጣ ። መገንጠል የሚለው መርህ አንደኛውና ዋናው ነው ቢባል ትክክል ነው ።

ለለውጥ የታገለውን ትውልድ ሀገር አስገነጠለ ብለው አሁንም ማውገዝ የሚቀናቸው አሉ ። ያለማወቅ ጉዳት ነው ተንኮል አዘል ባልሆነበት ። የኢትዮጵያን የብሄረሰብ/ ኤርትራን ችግር የፈጠረውና ያባባሰው ያ የታገለው ትውልድ ሳይሆን ስርዓቶቹ ናቸው ። የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ለስር ነቀል ለውጥ ሊታገል የተነሳው መሬት ለአራሹ መፈክርን አንግቦ ሲሰለፍ ማለትም በ1958/1965 ነው ። ከዚያም በኋላ ድህው ይማር፤ድህነት ወንጀል አይደለም፤ የሙብት እገዳው ይወገድ፤ በአርሶ አደሩ ላይ ጎጂ ግብር አይጣልበት ወዘተ ብሎ ከተሰለፈ በኋላ ነው ተማሪው ችግር ሆኖ የመጣውን የብሔረሰብ ጥያቄ መልስ ሊሰጥ የሞከረው ። ከዚህ ሁሉ በፊት፤ራሱ የተማሪው እንቅስቃሴ የሥር ነቀል ለውጥን አማራጭ ከመያዙ በፊት ማለትም በ1960 (በአውሮጳውያን አቆጣጠር) ጀምሮ የኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባር ቅኝ ግዛት ነን ብሎ የትጥቅ ትግሉን ጀምሮ ነበር ። ቀደም ብሎም በባሌ፤በኦጋዴንም ብሄረሰብ ጥያቄን የሚጠቅሱ አመጾች ነበሩ ። አንድ አደራጅ ድርጅት መስርቶ ወደፊት ለመጓዝ ይህንን ከፋፋይ ጥያቄ ምላሽ መስጠቱ ቅንጦት ሳይሆን ግዴታ ነበር ማለትም ይቻላል ። ከኤርትራ የመጡ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ጉዳይ አይመለከተንም እያሉ ከሰልፎች የሚርቁበት ጊዜ ነበር ። የኦሮሞ የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ (ቦምብ የፈነዳበት በአዲስ አበባ ና እነ ማሞ መዘምር የተሰቀሉበትም) አንደምታው ቀላል አልነበረም ። ዛሬ የታሪክ በራዦችና ያለፈን ካጆች ምንም ጭቅና አልነበረም ሊሉን ቢቃጡም ያፈጠጠና ያገጠጠ ልዩነት ነበር ። ኢትዮጵያ ለቡዝሃኑ እስር ቤት ሆነች ሲባል የባዶ ቃል ድርድረና ቃለ አጋኖነትም አልነበረም ። ዓይን ያለው ይህ፤ጆሮ ያለው ይስማ በተባለው መሰረት ወጣቶች ዓይን ጆሮአቸውን ከፍተው የወገንን ሰቆቃ ሰሙ፤ መከራውን አዩለት ። ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ያደረጉትን ፍለጋ የነበራቸው ርዕዮት ቢቃኘው የሚያስገርም አይሆንም ።

ይህን ሁሉ ቢነገሩ ቢነገሩ መረዳት የተሳናቸው ግን ተማሪዎች፤ ያ ትውልድ፤ ኢሕአፓ ሀገር አስገነጠሉ ይላሉ --ኤርትራን ያስገነጠለው ወያኔ፤ ለግንጠላ ያመቻቹት ደግም ቀደም ያሉት አገዛዞች መሆናቸውን በመካድ ። ተማሪዎችና ወጣት ተራማጆች ለምን ወደ ግራ አዘነበሉ? ለምንስ የቀኙና የአሜሪካ አዳናቂዎች ደከማ ሆኑ? ይህ  የሚመለሰው በዛሬ መነጽር ሳይሆን የነበረውን ሁኔታ በጊዜው ክልል በመመርመር ነው ። በዚያን ጊዜ ምዕራቡ ዓለም የብዝበዛና ጭቆና ማዕከል፤ የአፓርታይድና የዘረኝነት ደጋፊ፤ የአፍሪካ አምባገነኖች ቀኝ እጅ በመሆኑና በተጻራሪው ደግሞ የሶሻሊስቱ ጎራ ጸረ ቅኝ አገዛዝ ትግሎችን ይደግፉ ስለነበር ለውጥና ነጻነት ፈላጊዎች በአስተሳሰብ ወደ ሶሻሊዝም/ማርክሲዝም ማዘነበላቸው የሚጠበቅ ነበር ። የቬትናም/ኢንዶቻይና ትግሎች፤ የኩባ ትግል ድል፤ በደቡብ አሜሪካ የነበሩ ጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግሎች፤ ካብራል ሞንድሌን፤ ሉሙምባ  ንክሩማህ፤ አልጄሪያ የመን፤ ፓለስታይን፤ ማኦ ማኦ በኬንያ፤ ፌሊክስ ሙሜና ዩፒሲ በካሜሮን ወዘተ ወዘተ በየአቅጣጫው  የነበሩ የሕዝብ የነጻነትና የሙብት ትግሎች ።   አሜሪካ የደቡብ አፍሪካ ሕዝብን ትግልንና ራሱን ማንዴላን ሽብርተኛ የምትልበት ዘመን ማለት ነው ። ማን ሉሙምባን አስገድለ? ካብራልን ? ማሼልን? ሙሜና ዩዋንዴን? ኪማቲን? ዘመኑ የሕዝብ አመጽና የጸረ ቅኝ አገዛዝን ጸረ ኢምፐኢሪያሊስት ትግል ዘመን ነበርና ወደ ግራው ርዕዮት ያዘነበሉት ተማሪዎችና ወጣቶች--ወይም ያ ትውልድ-- ለብሄረሰብ ችግር የሰጠው መልስ በርዕዮቱ መሰረት ሆኖ እስከ መገንጣል የሚለውን ሙብት ማወቅ የሚለውን አጠቃለለ ። ይህን ሙብት ማወቅ ግን መገንጠልን በደፈናውና በግድ መደገፍ አይደለም የሚለውን መርህ የዛሬዎቹ ተቺዎች ባይረዱትም ተገንጣዮቹ ግን--በተለይ ሻዕቢያ-- የመገንጠል ሙብትን ማወቅ ነጻነታችንን መደገፍ ማለት አይደለምና ኢሕአፓ ነጻነታችን ተጻሯል በማለት ሲያወግዝ የነበረውን በቅርቡም ዳግም ገልጾታል ። ሶማሊያም የመስፋፋት አቅዋሟን ድርጅቱ ስላወገዘ ስላልተቀበለ በጠላትነት ፈርጀ እነ ወያኔን ረድታለች ። በአጭሩ ተገንጠሉ ተበታተኑ  አልተባለም ። ወያኔም በ1967 ልገንጠል ና ነጻን ትግራይን ልመሰርት የሚል መርሃ ግብር ሲያወጣ ኢሕአፓ ተቃወመው እንጂ አልደገፈውም ። ወደ ደርግ ውድቀት ገደማም ድርጅቱ ባወጣው የአዋም መግለጫ የፌዴራልን መፍትሄ አቅርቦ በሻዕቢያም በወያኔም ትምክህተኛ ብሎ መወገዙ በጽሁፍ ሳይቀር የሰፈረ ነው ። በአጭሩ ክስ ደረዳሪዎች ያለማወቅና ወይ አውቆ የማደናገር ተውሳክ የተጠናወታቸው ናቸው ማለት ይቻላል ።

ግንጠላ መዘዙ ብዙ ነው ። ምእራባውያን ይህን አማራጭ የሚገፉት ሀገሮችን ለማዳከምና ለመበታተን ነው ። በሶቬየት ህብረትና በዩጎዝላቪያ ላይ ተሞክሮ ያደረሰውም ጉዳትና መዘዝ የሚስተው  ይኖራል ማለት የሚቻል አይደለም ። ወደ ቅርባችን መለስ ስንል ኤርትራና ደቡብ ሱዳንን እንደ ምሳሌ መጥቀስ እንችላለን ። ጸሓይና በሪኻ ብሎ የጨፈረው ኤርትራዊ ሁሉ ዛሬ ደረቱን በሀዘን እየደለቀ መሆኑ ግልጽ

ነው ። በቅርቡ እንድ ታዋቂ ኤርትራዊ ምሁር ኤርትራ ሞታላች ገዳይዋም ቀባሪዋም ሻዕቢያ ነው ያለው ሀቅን መሰረት ያደረገ ግምገማ ነው ተብሏል ። ብዙ ሀተታ ሳናበዛ ኤርትራ ተገንጥላ ያገኘችው ጥቅም አንዱን አምባገነን በባሰ መተካት እንጂ ሌላ አለመሆኑን ሞትን በስደት የሚጋፈጡ ወጣቶች በአቅዋማቸው እያረጋገጡ ናቸው ። መገንጠሉ ጎዳ እንጂ አልጠቀመም፤ ስድስት ሚሊዮን ሕዝብን ወደ እንጦርጦስ ከተተ እንጂ ገነት አላገባቸውም ። ይህንን የመገንጠል ሂደት ምዕራቦች--በተለይም አሜሪካና እንግሊዝ-- እንደደገፉ ደግሞ የሚታወቅ ነው ። ካፈርኩ አይመልሰኝ ካልሆነ ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ ጽቡቅ ነው የሚሉ ኤርትራውያን ብዙ አለመሆናቸው የሚገመት ነው ። በሳምንት በሺ ደረጃ ሰው ሲሰደድ አለምክንያት አይደለም ። ሞት መኖሩን እያወቁ ሲሰደዱ ቢብስባቸው ነው ። ትግሉን መራን ያሉ ዛሬ በብረት ኮንተይኔር/ሳጥን ታጉረው ይሰቃያሉ ፡፤ የሞቱትም ብዙ ናቸው ። ያ የተዘፈነለት ሐርነት መና ቀርቷል ። ጸሓይ ጠለቀች እንጂ አልወጣችም ለኤርትራ።

ወደ ደቡብ ሱዳን ስናይ ደግሞ የደቡብ ሱዳን ሕዝብ በሰሜኖቹ ከኒሜሪ እስከ በሺር ባሉ አሀዛዦች መሰቃየታቸውና ዜግነትም መነፈገቻው በገቢር የሚታወቅ ነው ። አረቦቹ ደቡቦቹን ሕይዋኒን/እንስንሳት እያሉ ያደረሱባቸው ጥቃትና ውርደት ወደ ግንጠላ ቢገፋቸው የሚያስገርም አልነበረም ። የካርቱሙን አገዛዝ የጠሉት አሜሪካና አጋሮቹ--በተለይም እስራኤልና እንግሊዝ-- የደቡብ ሱዳን አመጽ ወደ መገንጠል ጎዳና እንዲገባ የተቻላቸውን አድርገዋል ። ምዕራባውያን በአፍሪካ ገዘፍ ያሉ ሀገሮችን (ናይጄሪያ፤ኮንጎ፤ ኢትዮጵያ፤ሱዳን ወዘተ) መከፋፈልና ማዳከም ይጠቅመናል ብለው የተያያዙት ስምሪት በመሆኑ ደቡብ ሱዳንን መገንጠል ይሁነን ብለው የያዙት ተልዕኮ ነበር ። ይህን በመቃወም ደረጃ የአማጽያኑ መሪ ኮለኔል ጆን ጋራንግ የተባባረች አዲስ ሱዳንን መመስረት የሚል ግብ ይዞ በመቆየቱና በዚህ ላይ አቋም በመያዙ በሄሊኮፕተር አደጋ (እንግሊዝ፤ዩጋንዳና አሜሪካ ባሉበት ሴራ) ተገደለና ለአሜሪካው ሎሌ ለሳላቫ ኪር ቦታው ተዘጋጀ ። የደቡብ ሱዳንም ሆነ የኤርትራ ልዩ የጋራ ብሔራዊ ማንነት ራሱ--ከዲንካ ኑዌር፤ ከትግራዊ በኒአምር ለሚለው በተለየ--ደማቅ ህልውና ያለው መሆኑ አከራካሪ በመሆኑ ደቡብ ሱዳን ከጎጥ/ብሄረሰብ አልፎ ሀገራዊና ብሔራዊ ማንነት ሊከሰት ባለመቻሉ እነሆ ጎሳን መሰረት ያደረገ ጦርነትና ግድያ ተፋፍሞ አለ ። በዚህ ላይ ደግሞ ደቡብ ሱዳን የቤንዚንና የለም መሬት ባለቤት በመሆኗም ቀውሷ መባባሱ አልቀረም--እንደ ዛይር/ኮንጎ ። ደቡብ ሱዳን እንደ አንድ ሀገር ህልውና ይኖረዋል ወይ ለሚለው ጥያቄና ስጋት የሚያረጋጋ ምላሽ ለመስጠት ማንም የሚደፍር የለም ።

የተነሳንበት ዋና ቁም ነገር መገንጠል ጠቃሚ ሳይሆን ጎጂ ነው/ነበርም የሚለውን ጫና ሰጥቶ ለማቅረብ ነው ። የአፍሪካንም ሆነ የሌሎቹንም ተመክሮና ተጨባጭ ሁኔታ ማንሳት የተገደድነው ለዚሁ ነው ። ይህ

በዚህ እንዳለና ሀቅ ሆኖ እየተገኘ እንደ ኦነግ አይነቶቹ አሁንም መገንጠል በሚል አጓጉል አባዜ ተይዘው መቆየታቸው የሚያሳዝን ሆኖ ይገኛል ። ወያኔም ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ለብቻ ለማድረግ አሊያም ከኤርትራ በትግራይ ትግሪኚ ደረጃ ለማዋሀድ የሚመኘው ከንቱ ሆኖ የሚቀር መሆኑ ከወዲሁ የሚታወቅ ነው ። ኤርትራ  ተገንጥላ ተመቻች ጫጫች? ዜጎቿ አለፈላቸው ወይስ የባሕር ሰለባ ሆነው አለቁ? ደቡብ ሱዳን በራስ አገዛዝ መቆየትን ትታ በ ባእዳን ግፊት ተገንጥላ ሀገር ሆነች ወይስ ሕጻናቷን ሳይቀሩ የምትጨፈጭፍ ጉድ ሆነች? መልሱ ለማንም ህሊና ያለው ዜጋ ግልጽ ነው ።